# የተማሪዎች የፅሁፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎችና መንስኤዎች በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም መስተዳደር ዞን አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

Gebeyehu Shiferaw ፣ Mollalign Tameru*

Eduacational planning and management, Instutute of Educational and Behavioural Sciences, Debre Markos University, Debre Markos, P.o.B 269, Ethiopia.

*Corresponding Author Email: molalignfikru@gmail.com, molalegne_tamiru@dmu.edu.et

**አጽህሮተ ጥናት**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም ዞኖች አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትም/ት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ላይ የሚታየውን የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎችና መንስኤዎችን መፈተሽ ነው፡፡ የአጠናን ስልቱ ገላጭ ምርምር ሲሆን አይነታዊና መጠናዊ የጥናት አቀራረቦችን ተጠቅሟል፡፡ የጥናቱ ወሰን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም መስተዳድር ዞን ከሚገኙ 38 ወረዳዎች ውስጥ 12 አጠ/2ኛ ደረጃ ትም/ት ቤቶች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በዚህ የጥናት ወሰን ውስጥ መጠናዊ መረጃዎች በዝግ የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ ሲሆን ተሳታፊዎችም መምህራንና ተማሪዎች ነበሩ፡፡ አይነታዊ መረጃዎች ደግሞ በልቅ የጽሑፍ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በገጽ ለገፅ ቃለ ምልልስ ተሰብስበዋል፡፡ በዚህ በአይነታዊ መረጃ ስር በልቅ የጽሑፍ መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት መምህራንና ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን የትም/ት ቤት ርዕሰ መምህራን በገፅ ለገፅ ቃለ ምልልስ መረጃ ሰጠዋል፡፡ በዝግ የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ወደ መቶኛ በመቀየር፣ በአይነታዊ የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ ገለፃዊ በሆነ መንገድ ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የኩረጃን አስከፊነት ግንዛቤው ቢኖርም እንደቀላል ጉዳይ በመመልከት ልማድ እየሆነ መምጣቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የጽሑፍ ኩረጃዎችን በመጠቀም እንደሚሰሩ ውጤቱ ያሳየ ሲሆን ዋናዋናዎቹ ከጎን ካለ ጓደኛ በመውሰድ፣ መልስ በቁራጭ ወረቀት በመቀያየር፣ መግባቢያ ኮድ በመጠቀም፣ በተለያዩ ነገሮች ላይ በመጻፍና በሞባይል ስልክ መልዕክት በመለዋወጥ ናቸው፡፡ ለዚህ ሁሉ ችግር መነሻ ምክንያቶች ደግሞ የተማሪዎችን በቁጥር ብቻ የሚገለፅ ውጤት እንደመስፈርት በመጠቀም ተገቢ ያልሆነ ውድድር፣ የትምህርት ቤት አመራሮችና ወላጆች ክትትል ማነስ፣ የመምህራን ብቃትና ግዴለሽነት፣ ውጤታማ ተማሪዎችን ያለማበረታታት፣ ምቹ የትምህርት አካባቢ ያለመፍጠር ይጠቀሳሉ፡፡ በአጠቃላይ የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ በተለይም እንደእኛ ባለ ደሃ ሀገር ውስጥ የህልውና ጉዳይ ተደርጎ ካልተወሰደና መፍትሔ ካልተበጀለት እየመጣ ያለው መዘዝ እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ በመጨረሻም ግኝቶችን መሠረት በማድረግ መንግስት/ትምህርት ሚኒስቴር ኩረጃን ለመከላከል ፖሊሲና ህግ በማውጣት ተግባራዊ ቢያደርግ፣ በቁጥር ብቻ የሚገለፅ ውጤት ላይ ብቻ ያተኮረ የተማሪዎች ውድድር ቢፈተሽ፣ የሚሰሩና ውጤታማ የሆኑ መምህራንና ተማሪዎች የሚበረታቱበት ስርዓት ቢፈጠር፣ ትምህርት ቤት አመራሮችና ወላጆች ክትትል ቢጠናከርና ለትምህርት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቢሟሉ የሚሉ ምክረ ሀሳቦችን አቅርቧል፡፡

*<u>ቁልፍ ቃላት:</u> አጠቃላይ ሁለተኛ ድረጃ ትቤት ፣ ፈተና፣ ዘዴዎችና መንስኤዎች ፣የጽሁፍ ፈተና ኩረጃ*

## 1. መግቢያ

የተማሪዎች የፅሁፍ ፈተና ኩረጃ አመለካከት፣ ዘዴዎችንና መንስኤዎች አስመልክቶ በተደረገው ጥናት ስር የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ መነሻ ችግሮችና ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመሰረታዊ ቃላትና ሃረጋት አጠቃቀም ብያኔዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ምሁራን ኩረጃን "የአካዳሚክ ማጭበርበር" የሚል ስያሜ ይሰጡታል (Anteneh Assefa and Asres Berhan ፣ 2014):: ትርጉሙም የሌሎችን የአካዳሚክስ ሥራ ሳያስፈቅዱ ባለቤት ለመሆን መሞከር ወይም የፈተና ውጤት መቅዳት ማለት ነው፡፡ ይህም በቃል፣ በምልክት፣ በፅሑፍ፣ ቴክኖሎጅንና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ሊከናወን እንደሚችል ይጠቅሳሉ (Trevino, 2006፤ Thibodeau, 2007)፡፡ ኩረጃ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ወይም እርከኖች የሚከሰት የአለም አሳሳቢ ችግር በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ Aurora, Teixeira and Rocha (2008) በስፔንና ፖርቹጋል ባካሄዱት ጥናታቸው እንደገለፁት ኩረጃ የሁሉም አገር የጋራ ችግር እየሆነ የመጣ ሲሆን በተለይም የቴክኖሎጅ ማደግ ደግሞ ችግሩን የበለጠ እያወሳሰበው እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡ በተጨማሪም Lupton & Chapman (2002) በአሜሪካውያንና ሩሲያውያን ኮሌጅ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ኩረጃ በትምህርት ጥራት ላይ በሚያስከትለው ችግር ብቻ ሳይሆን በማይኮራረጁ ተማሪዎች ላይም የሚያደርሰው በደል እየከፋ በመምጣቱ በተማሪዎች የእውቀትና የክህሎት ምዘና ውጤት ላይ የተሳሳተ መረጃ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በኩረጃ ምክንያት ጥራቱ የተጓደለ የትምህርት ውጤት በተመዘገበ ቁጥር በሥራ ቦታ ለሚፈጠረው የአቅም ማነስ ብሎም በሀገር ላይ ለሚከሰተው የምርትና አገልግሎት ጥራት መቀነስ መነሻ ይሆናል፡፡

በፈተና ጊዜ መኮረጅ በትምህርት ሂደት፣ በማህበራዊና በስነ-ልቦና ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ Hamzeh (2012) ሲገልፁ፤ ኩረጃ ከትምህርት አንፃር ሲታይ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ያላቸውን ተስፋ ያሳጣል፡፡ በተለይም ተማሪዎች መከተል የሚገባቸውን መልካም እሴቶችና ቀና አመለካከቶች ይሸረሽራል፡፡

የኩረጃ ተፅዕኖ በሚኮረጁ ተማሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተማሪዎችም ሚዛናዊ ያልሆነ አስተሳሰብ ይዘው እንዲያድጉ መሠረት የሚጥል ነው (Lanier,2006፤ Wilson, 2008)፡፡ ምናልባትም በጣም የከፋው ደግሞ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከጨረሱ ወይም ከተመረቁ በኋላ የማጭበርበርና ሳይሰሩ ባቋራጭ የመክበር ባህሪያቸው በህይወታቸው ሙሉ እንዲቀጥሉበት መንገድ መክፈቱ ነው፡፡ ከሥነ ልቦና አንፃር ያለውን ችግር ሀምዚህ በመጨረሻ ሲያጠቃልሉ፣ ኩረጃ ተማሪዎች የተረጋጋ ህይወት እንዳይኖራቸው ምክንያት በመሆን በራስ የመተማመን ስሜታቸውን ያሳጣል፡፡ ኩረጃ ትምህርት ቤቶች ብቁና ሀገር ገንቢ የሆኑ ዜጎችን የማፍራት ህልማቸውን በማጨናገፍ ለሙስና በር ከፋች የሆኑ ዜጎችን የሚያፈሩ ተቋማት እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል (Vandehey, Diekhoff, & LaBeff, 2007)፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ለራሳቸውና ለሌሎች የሚሰጡትን ክብር፣ ለህሊናቸው መታዘዝን ፣ የመማር ፍላጎታቸውንና የመማር አቅማቸውን ያጓድላል (Zauwiyah, Maimun & Junaini,2008)፡፡

Mahmoud & Fatima Al-Shaikh (2013) ኩረጃ አንዳንድ ተማሪዎች ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላ የክፍል ደረጃ ለማለፍ ከሚጠቀሙበት ጎጅ ልማዶች ዋነኛው መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ሁልጊዜ አዳዲስ የኩረጃ ዘዴዎችን ሲፈልጉ ፈታኞች (መምህራን) ደግሞ ኩረጃን ለመቆጣጠር የተለያዩ መፍትሔዎችን ሲቀይሱ የአይጥና ድመት አይነት መደባበት የሚታይበት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ብዙ ምሁራንም በጉዳዩ ላይ ሲወያዩና የኩረጃ መንስኤዎችንና መፍትሔዎችን በማጥናት

ሰፊ ጥረት አድርገዋል (McCabe and Drinan,1999፤ሪቻርድ፣2009) ፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ኩረጃን በረቀቀ መንገድ ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩትም የኩረጃ ዘዴዎች በየጊዜው እየተቀያየሩ በመምጣታቸው ምክንያት የመከላከያ ዘዴዎችም የበለጠ ትኩረት እንዲሰጥባቸው ያመለክታል፡፡ Coalter, Lim, & Wanorie (2007) በወቅቱ ባደረጉት ጥናት የተወሰኑ የኩረጃ ዘዴዎችን መጥቀስ ሞክረው ነበር፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በሞባይል መላላክ፣ በቁርጥራጭ ወረቀት፣ በማስመሪያ፣ በወንበር ወይም በዴስክ፣ በእጅ ወይም በልብስ በመፃፍ የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከፊት ወይም ከጎን ከተቀመጠ ጓደኛ በመቅዳት እንዲሁም ሽንት ቤት በመሄድ ያዘጋጁትን መረጃ በመጠቀም እንደሚኮርጁ አረጋግጠዋል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እየተስፋፋ ያለውን ኩረጃ ምሁራን በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብና በሃገር ላይ የሚያስከትለዉን ጉዳት በጽሁፋቸው በሰፊው አስገንዝበውናል፡፡ ስለዚህ ይህን ችግር ለመከላከል ወይም ለመቀነስ በየጊዜው የተለያዩ ጥናቶችን እየሰሩ መፍትሄ ማፈላለግ ለነገ ተብሎ የሚተዉ ተግባር አይደለም፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግሮችና ጥያቄዎች

ኩረጃ በተለያዩ የትምህርት እርከኖች በሚዘጋጁ የፅሑፍ ፈተናዎች የተለመደ እየሆነ መምጣቱን በመግቢያው ላይ የተጠቀሱ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ኩረጃ በማንኛውም የምዘና ዘዴ (የቤት ሥራ፣ የፕሮጀክት ሥራ፣ የጥናት ፅሑፎችና የላብራቶሪ ሪፖርቶች) የሚከሰት ቢሆንም በፅሑፍ ፈተና ጊዜ ኩረጃ የበለጠ ጎልቶ ይታያል (Graves, 2008)፡፡ የዚህ ዋና ምክንያት ደግሞ በእኛ አገርም ሆነ በሌሎች አገሮች ያለው የትምህርት ስርዓት በአብዛኛው የተለመደው የምዘና ዘዴ የፅሑፍ ፈተና ስለሆነ ነዉ (Okoro, 2001)፡፡ በፈተና ጊዜ ኩረጃ በሀገራችን በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመደረሱ ምክንያት የትምህርት ሚኒስቴርና ክልል ትምህርት ቢሮ በተለያየ ጊዜ በማስታወቂያ መልክ የሚያስተላልፉት መልዕክት በዋቢነት ሊወሰድ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን የፈተና ኩረጃ ለመከላከል በፈተና ጊዜ አንዳንዶችም ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ በማንኛውም ጊዜ ሞባይል ይዘው እንዳይገቡ ህግ በማውጣት ሲጠቀሙ ይታያል፡፡

Anteneh Assefa and Asres Berhan (2014) በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ባደረጉት ጥናት ኩረጃ በመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች የተለመደ ችግር እንደሆነና የዚህ መነሻም ከዚህ በፊት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት ኩረጃን በመለማመዳቸው አሁንም ልምዱ የቀጠለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሌላው Abdulah Muhammed (2014) በሶማሊያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማጥናት የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ ዋና ዋና ምክንያቶች ብለዉ ያቀረቡት፤ በደንብ ያለማጥናት፣ ከፍተኛ ውጤት መፈለግ፣የፈታኝ መምህራንና የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ወይም ርዕሰ መምህራን ትኩረት ሰጠ ያለመከታተል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ምንም እንኳን ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች የኩረጃ ችግር ምን ያህል የገዘፈ እንደሆነና በተወሰነም ደረጃም ቢሆን ምክንያቶችን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ነገር ግን የችግሩን መንስኤ (root cause) በጥልቀት አልመረመሩትም፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ለፈተና በደንብ አጥንተው ለምን እንደማይዘጋጁ እንዲሁም መምህራንና አስተዳደሩ ለምን ትኩረት እንዳልሰጡ በጥልቀት አላዩትም፡፡ በጥናታቸው የመረጃ

መሰብሰቢያ መሳሪያም ቢሆን ተማሪዎችንና መምህራንን ያሳተፉት በፅሑፍ መጠይቅ ብቻ በመሆኑ በጥልቀት ያዩት አይመስልም፡፡ በተጨማሪም ከኩረጃ ጋር በተያያዘ በትምህርት ቤቶች ያለውን ህግና ደንብ ፈትሸው ክፍተቱን አላወጡም፡፡ ከዚህ ባሻገር የኩረጃ ዘዴዎች በተወሰነ ጊዜ በተካሄዱ ጥናቶች መነሻ ብቻ መከላከል ስለማይችል በየጊዜው እየተቀያየረ የመጣውን የኩረጃ ዘዴ በየወቅቱ እያጠኑ መፍትሔ ማፈላለግ ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ አጥኝዎች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ አሳማኝ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በፊት በተጠኑ ጥናቶች ያልታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር አድርገዋል፡፡

በመሆኑም በሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎች መሪነት ጥናቱ ተሠርቷል፡፡

1. በአሁኑ ወቅት የተለመዱ የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
2. የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?

## 2. የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የተከተለው የአጠናን ስልት ገላጭ ምርምር ሲሆን የጥናቱ አቀራረብም መጠናዊና አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ይህ ስልት የተመረጠበት ምክንያት በአንፃራዊ በዛ ካሉ ናሙናዎች መረጃ በመሰብሰብ በአሁኑ ወቅት ያለውን የኩረጃ ተግባር በማብራራት ለማጥናት ስለሚያስችል ነው (Burns, 2000) ፡፡ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚገኙትን በመተንተን ተገልጿል፣ የተደረሰበት ማጠቃለያም ቀርቧል፡

### 2.1. የናሙና አመራረጥና ተሳታፊዎች

ጥናቱ ያተኮረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም ዞን በሚገኙ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ነው፡፡ በጥናቱ የተካተቱ መረጃ ሰጪዎች፣ ተማሪዎች፣ መምህራንና፣ ርዕሰ መምህራን ነበሩ፡፡ ጥናቱ የእድል ሰጪ ንሞና ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎችና መምህራንን በተራዘመ ወይም ተደጋጋሚ ንሞና ተመርጠዋል (ያለዉ፣ 2011)፡፡ በዚህም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ካሉ ዞኖች ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቅርብ ከሆኑት በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም የሚገኙ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተወስደዋል፡፡ በ2010 ዓ.ም ምስራቅ ጎጃም ዞን 19 ወረዳዎች 41 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ምዕራብ ጎጃም ዞን 19 ወረዳዎች 39 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሏቸው፡፡ ከእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ከእያንዳንዱ ዞን 6(30%) ወረዳዎች በድምሩ 12 ወረዳዎች በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ ተመርጠዉ የተካተቱ ሲሆን ከእያንዳንዱ ወረዳ አንድ አንድ ትም/ቤት በጠቅላላ 12 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ በናሙናነት ተመርጠዋል፡፡ በነዚህ ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ ዘጠና ስድስት መምህራን ተመርጠዋል፡፡ በተመሳሳይ ዘዴ አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ተማሪዎች ተመርጠዉ መረጃዉ ተሰብስቧል፡፡ ፡፡ በመቀጠልም ከየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ በአጠቃላይ አስራሁለት ርዕሰ መምህራን ካላቸው የስራ ድርሻ

ተገቢነትና ልምድ አንፃር ዓላማ ተኮር ወሳኝ ንሞና በመጠቀም ተመርጠዋል (Best and Kahn,2007)፡፡

### 2.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኙ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፡- የቡድን ተኮር ውይይት፣ የገጽ ለገፅ ቃለመጠይቅ፣ የፅሁፍ መጠይቅና የሰነድ ምርመራ ነበሩ፡፡ ተማሪዎችና መምህራን በፅሁፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት በመሳተፍ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በኩረጃ ዘዴዎች ና መንስኤዎች ዙሪያ ለተዘጋጁት መጠይቆች የታማኒነት ፍተሻ በሃያ መምህራንና ሃያሁለት ተማሪዎች ተከናዉኗል፡፡ የክሮንባክ አልፋ ዉጤት 0.81 ና 0.83 በተከታታይ የተገኘ ስለሆነ ተአማኒነታቸዉ በጥሩ ደረጃ ላይ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅመንባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የመጠይቆች ተገቢነት ለሙያዉ ቅርብ በሆኑ ሙህራን አማካኝነት ማረጋገጫ ተስጥቶበታል፡፡ ሁለት (አንድ የመምህራን አንድ የተማሪዎች) የቡድን ተኮር ዉይይቶች ተከናዉነዋል፡፡ በቡድን ተኮር የተሳተፉ መምህራን የተመረጡት ባላቸዉ ከፍተኛ አገልግሎት ዘመን ሲሆን ተማርዎች ደግሞ በዉይይት መሳተፍ ይችላሉ ተብለዉ በተማሪዎች የተመረጡ ናቸዉ፡፡ በእየንዳንዱ የቡድን ተኮር ዉይይት አስራሁለት ተወያዮች ተሳትፈዋል፡፡ እርዕሰ መምህራን በገጽ ለገጽ ቃለ ምልልስ ተሳትፈዋል፡፡ በሰነድ ምርመራም ከኩረጃ ጋር በተያያዘ የወጡ ህግና ደንቦች ተተንትነዋል፡፡

### 2.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

መረጃ ሰብሳቢ ባለሙያዎችና በአጥኝዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተቀመጠላቸው አላማዎች አንፃር ተተንትነዋል፡፡ በዝግ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመቶኛ ተቀይረዉ ተገልፀዋል፡፡ ይህ ስታትስቲካዊ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ሁሉም አንባቢዎች በቀላሉ እንዲገነዘቡትና የተሰጡ ምላሾችን ለማነጻጸር ስለሚያስችል ነዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በልቅ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይት፣ በቃለመጠይቅና ከመዛግብት የተገኙ መረጃዎችን ላንባቢ የቀረቡት ትረካዊ ወይም ገለጣዊ መንገድን በመከተል ነዉ፡

## 3. የጥናቱ ትንተና

በዚህ ክፍል ውስጥ መረጃዎች ተደራጅተው የሚቀርቡበትና የሚተነተኑበት ነው፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች በቁጥር የተሰበሰበው መረጃ በሰንጠረዥ ተደራጅቶ በመተንተን የተገኘው ውጤት ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በልቅ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይቶች በቃለ ምልልስ የተገኙ መረጃዎችን ትረካዊ ወይም ገለፃዊ በሆነ መንገድ ተብራርተዋል፡፡ በጽሑፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት መምህራንና ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን የገፅ ለገፅ የቃለ መጠይቅ ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ጋር ተከናውኗል፡፡ የጥናቱ ግኝቶች የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ በየንዑስ ርዕስ በመከፋፈል ቀርቧል፡፡ መረጃ ሰጭዎች የእድል ሰጭ ንሞና ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎችንና መምህራንን በተራዘመ ወይም ተደጋጋሚ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ በዚህም ለመረጃ ሰጭነት ከተመረጡ 96 መምህራን የፅሑፍ መጠይቅ ተበትኖ 85 መምህራን (88.5%) ሞልተው መልሰዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለ159 ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ተሰራጭቶ 137 ተማሪዎች (86.2%) ሞልተው መልሰዋል፡፡ ከምስራቅና ምዕራብ ጎጃም ከተመረጡ 12 አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ጋር በተደረገ የቃል ምልልስ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች ለየብቻቸው

ከሁለት ቡድን በማደራጀት ተወያይተው መረጃ ሰጥተዋል፡፡

### 3.1. የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎች

**ሠንጠረዥ 1፡- በፅሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎች ዙሪያ ከመምህራንና ተማሪዎች የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | በፈተና ወቅት ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የኩረጃ ዘዴዎች | መምህራን | | | | | | ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በአብዛኛው | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ | | በአብዛኛው | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | አልፎ አልፎ | |
| | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 1 | ቴክኖሎጅን ወይም ሞባይል መጠቀም | 14 | 16.5 | 9 | 10.6 | 62 | 72.9 | 25 | 18.2 | 17 | 12.4 | 95 | 69.3 |
| 2 | በቁራጭ ወረቀት መልስ ይዞ መግባት ወይም መለዋወጥ | 75 | 88.2 | 2 | 2.4 | 8 | 9.4 | 108 | 78.8 | 9 | 6.6 | 20 | 14.6 |
| 3 | አንዳድ መረጃዎችን በእጅ ወይም በሌላ የሰውነት አካል ላይ፣ በወንበር፣ በጠረጴዛ፣ በልብስ፣ በግድግዳ መፃፍ | 53 | 62.4 | - | - | 32 | 37.6 | 53 | 38.7 | 3 | 2.2 | 81 | 59.1 |
| 4 | አጠገብ ያለ ጓደኛን መጠየቅ ወይም ከጎን ካለ ጓደኛ መገልበጥ | 74 | 87.1 | 1 | 1.2 | 10 | 11.8 | 104 | 75.9 | 6 | 4.4 | 27 | 19.7 |
| 5 | አመመኝ ወይም ሽንት ቤት ልሄድ ነው በማለት የተዘጋጀ መረጃ ይዞ መመለስ | 12 | 14.1 | 17 | 20 | 56 | 65.9 | 19 | 13.9 | 30 | 21.9 | 88 | 64.2 |
| 6 | በጥቅሻ | 28 | 32.9 | 15 | 17.6 | 42 | 49.4 | 50 | 36.5 | 13 | 9.5 | 74 | 54 |
| 7 | የመግባቢያ ኮድ በማዘጋጀት | 31 | 36.5 | 19 | 22.4 | 35 | 41.2 | 42 | 30.6 | 16 | 11.7 | 79 | 57.7 |

በሠንጠረዥ1. ያለው መረጃ እንደሚያሳየው ተማሪዎች በጽሑፍ ፈተና ወቅት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችን በተመለከተ በአብዛኛው መምህራን (88.2%) እና ተማሪዎች (78.8%) በሰጡት ምላሽ በቁራጭ ወረቀት መልስ ይዞ መግባት ወይም መለዋወጥ ከፍተኛውን ድርሻ ሲይዝ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አጠገብ ወይም ከጎን ካለ ጓደኛ በመጠየቅ ወይም በመገልበጥ ነው ሲሉ 87.1% መምህራን እና 75.9% ተማሪዎች ምላሽ ሰጠዋል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች ከግማሽ በላይ ከሆኑ ምላሽ ሰጭዎች መምህራን (62.4%) የሚኮርጁ ተማሪዎች በሰውነት አካላቸው፣ በወንበር፣ በጠረጴዛ፣ በልብስ፣ በግድግዳ አስቀድመው በመጻፍ እንደሚጠቀሙ ያሳያል፡፡ በዚህ ነጥብ ዙሪያ ከግማሽ በላይ የሆኑ ተማሪዎች (59.1) አልፎ አልፎ እንደሆነና 38.7% ተማሪዎች የመምህራንን ሀሳብ ተጋርተዋል፡፡ ሌሎች ደረጃቸው ይለያይ እንጅ ሁሉም የጽሁፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎች እንደሚተገበሩ ስንጠረዥ ያስገነዝባል፡፡

መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ከዝግ መጠይቆች በተጨማሪ በልቅ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህም መምህራንና ተማሪዎች የሰጡት የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎች ሲጠቃለሉ በፈተና ወቅት አመመኝ ብሎ መጮህና ክፍሉን መረበሽ፣ በእጅ ጣት የፊደል ኮድ በመፍጠር መነጋገር፣ ጉንፋን የያዛቸው በማስመሰል በሶፍት አፍንጫቸውን እየጠረጉ በቁራጭ ወረቀት የተፃፈውን መጠቀም፣ መታወቂያ በመቀያየር የሌላ ሰው መፈተን፣ የፈተናውን ቁጥርና የምርጫ ፊደል በመናገር እንዲነበብ መጠየቅና በተዘዋዋሪ መልሶ መናገር፣ በእስክብሪቶ ክዳን የመልስ ወረቀት ጠቅልሎ ማስገባትና እስክብሪቶ መዋዋስ፣ ሁለት የክብሪት ቀፎዎችን በክር በማሰር የመልስ ወረቀቶችን

በማስገባት መለዋወጥ፣ ደብተር ወይም መፅሐፍ ይዞ መግባት፣ መልስ ወረቀት ጠቅልሎ በመወርወር፣ የተለያዩ ቀለም ያላቸውን እስክብሪቶዎች /እርሳሶችን እንደ ኮድ በመጠቀም መልስ መለዋወጥ፣ የጥያቄ ወረቀት ከመፈተኛ ክፍል በማውጣት መልሱን በቀጭን ገመድ /ክር ከውጭ ወደ ክፍል በማያያዝ ማስተላለፍ የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡

ከመምህራንና ከተማሪዎች በተጨማሪ ርዕሰ መምህራን በቃለ ምልልስ ስለ ጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎች ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚህም ከላይ የተጠቀሱትን የተጋሩ ሲሆን ከርዕሰ መምህራን መካከል አንዱ፡-

*“በአንድ ወቅት ለ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ለሱፐርቫይዘርነት ተመርጬ በሄድኩበት ትም/ት ቤት ሲፈተኑ በየክፍሉ ስዞር በነፋስ የምትንቀሳቀስ የምትመስል ቁራጭ ወረቀት አየሁ ትኩረት ሰጥቼ ስከታተል በክር ታስራ የምትጎተት መልስ የያዘች ወረቀት ነበረች፡፡”* (መጋቢት፥ 2010 ዓ.ም)

በማለት ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ለጽሑፍ ፈተና ኩረጃ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምን ያህል እየተወሳሰቡ እንደሄዱ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የተማሪዎች የፅሑፍ ኩረጃ ዘዴዎች በተመለከተ ከዚህ በላይ የተሰጡ ምላሾች እንደሚያስረዱን በአብዛኛው ተማሪዎች ለመማር ዓላማ ይዘውና ተዘጋጅተው ከመፈተን ይልቅ በየጊዜው የሚቀያየሩ የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎችን መጠቀም የመረጡ መሆኑን ያሳያል፡፡

### 3.2. የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤዎች

**ሰንጠረዥ 2. ለተማሪዎች የፅሑፍ ፈተና መኮራረጅ መንስኤዎች በተመለከተ**

| ተ.ቁ | የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤዎች | መረጃ ሰጭዎች | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መምህራን | | | | | | ተማሪዎች | | | | | |
| | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | |
| | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎች ለፈተና ስለማይዘጋጁና ስለማያጠኑ | 72 | 84.7 | 10 | 11.8 | 3 | 3.5 | 112 | 81.8 | 18 | 13.1 | 7 | 5.1 |
| 2 | የፈታኝ መምህራን ግዴለሽነትና አጉል ተወዳጅነት | 29 | 34.1 | 48 | 56.5 | 8 | 9.4 | 13 | 9.5 | 44 | 32.1 | 80 | 58.4 |
| 3 | ቤተሙከራ፣ ቤተ መፃህፍትና ኢንተርኔት ያለማሟላት | 12 | 14.1 | 27 | 31.8 | 46 | 54.1 | 11 | 8 | 69 | 50.4 | 57 | 41.6 |
| 4 | የመምህራን የማስተማር ብቃት ማነስ | 11 | 12.9 | 51 | 60 | 23 | 27.1 | 72 | 52.6 | 45 | 32.8 | 20 | 14.6 |
| 5 | የፈተና መክበድ | 8 | 9.4 | 60 | 70.6 | 17 | 20 | 84 | 61.3 | 36 | 26..3 | 17 | 12.4 |
| 6 | የትም/ት ቤቱ አስተዳደር የቁጥጥር ማነስ | 54 | 63.5 | 24 | 28.2 | 7 | 8.2 | 70 | 51.1 | 41 | 29.9 | 26 | 19 |
| 7 | ከኩረጃ ጋር የተያያዘ ጠበቅ ያለ ህግ ያለመኖርና ተግባራዊ ያለማድረግ | 69 | 81.2 | 13 | 15.3 | 3 | 3.5 | 104 | 75.9 | 25 | 18.2 | 8 | 5.8 |
| 8 | በአንድ ክፍል የሚፈተኑ ተማሪዎች ቁጥጥር መብዛት | 73 | 85.9 | 8 | 9.4 | 4 | 4.7 | 115 | 83.9 | 12 | 8.8 | 10 | 7.3 |
| 9 | የተማሪዎች የመማር ፍላጎት መቀነስ | 61 | 71.8 | 15 | 17.6 | 9 | 10.6 | 97 | 70.8 | 22 | 16.1 | 18 | 13.1 |
| 10 | እኔ ባልኮርጅ ሌሎች ይበልጡኛል ብሎ ማሰብ | 29 | 34.1 | 50 | 58.8 | 6 | 7.1 | 83 | 60.6 | 40 | 29.2 | 14 | 10.2 |
| 11 | ከክፍል ክፍል ማለፍን ብቻ ዓላማ ማድረግ | 58 | 68.2 | 22 | 25.9 | 5 | 5.9 | 90 | 65.7 | 31 | 22.6 | 16 | 11.7 |

በሰንጠረዥ 2 መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡት መምህራንና ተማሪዎች የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤዎች ምን እንደሆኑ መልስ እንዲሰጡ በተጠየቁት መሠረት 85.9% መምህራንና 83.9% ተማሪዎች የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤ በአንድ ክፍል የሚፈተኑ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት እንደሆነ በአንደኛ ደረጃ አስቀምጠዋል፡፡ በመቀጠልም 84.7% መምህራንና 81.8% ተማሪዎች የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ምክንያት ተማሪዎች ለፈተና ስለማይዘጋጁና ስለማያጠኑ እንደሆነ፣ በሶስተኛ ደረጃ ከፍተኛ መንስኤ ኩረጃ በሚፈፅሙ ተማሪዎች ላይ ጠበቅ ያለ ህግ ያለመኖርና ተግባራዊ ያለማድረግ እንደሆነ 81.2% መምህራንና 75.9% ተማሪዎች አረጋግጠዋል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች ውስጥ 71.8% መምህራንና 70.8% ተማሪዎች በሰጡት መልስ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት መቀነስ በአራተኛ ደረጃ ለኩረጃ ምክንያት ነው ብለዋል፡፡ ከክፍል ክፍል መዛወርን ብቻ ዓላማ ማድረግ በአምስተኛ ደረጃ መንስኤ ይሆናል በማለት 68.2% መምህራንና 65.7% ተማሪዎች መልስ ሰጠዋል፡፡ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች (61.3% ፣ 60.6%፣ 52.6%) ለኩረጃ መንስኤ ነው ያሉትን የፈተና መክበድ፣ እኔ ባልኮርጅ ሌሎች ይበልጡኛል ብሎ ማመን፣ የመምህራን የማስተማር ብቃት ማነስ እንደሆነ በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ መምህራን (63.5%) የትም/ት ቤቱና ሌሎች አመራሮች የቁጥጥር መላላት በስድስተኛ ደረጃ የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤ እንደሆነ ሲመልሱ 51.1% የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ የቁጥጥር መላላትን በሰባተኛ ደረጃ አስምጠዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መምህራንና ተማሪዎች የጽሑፍ ፈተና ከረጃ መንስኤዎችን በልቅ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ሀሳብ እንዲሰጡ ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚህም በመምህራን በኩል የተሰጠው ምላሽ ሲጠቃለል፣ ተማሪዎች እንዳይኮራረጁ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያደርግ መምህር ድብደባና ዛቻ ስለሚደርስበትና ዋስትና ያለመኖር የጽሁፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት አንዱ መምህር "እኔና ጓደኛየ እራት በልተን ስንመለስ በመንገዳችን ተደብቀው ቆይተው ሊደበድቡን ሲሉ ሮጠን አምልጠናል" በማለት ገልፀዋል፡፡ አንድ ሌላ የቡድን ተወያይ መምህርት ደግሞ "ተማሪዎችን ስፈትን በደንብ ተቆጣጥሬ በመያዜ ከክፍል ስወጣ ጠብቀው አንች ከሌላው መምህር በምንትለያለሽ ይህን ባህሪሽን ባታሻሽይ በራስሽ ፈርደሻል በሚል ዛቻና የሴትነት ሞራል የሚነካ ስድብ ሰድበውኛል" በማለት መረጃ ሰጣለች፡፡ ይህ የሚያሳየዉ አንዳንድ መምህራን በአግባቡ ለመፈተን ሲሞክሩ የደህንነት ስጋት ያለባቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በቡድን ውይይቱ አንድ ሌላ መምህርም የተወጋ የሂሳብ መምህር አውቃለሁ በማለት አስረድቷል፡፡

በየደረጃው ያሉ የትምህርት ሃላፊዎች ብዙ ተማሪዎች ሲያልፉ መሸለማቸው፣ በየዓመቱ የሚታቀደው የሚያልፉ ተማሪዎችን ቁጥር ማሳደግ እንጅ ምን ያህል ብቃት አላቸው በሚል ያለመሰራቱ ዋነኛው የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ምክንያት መሆኑን መረጃ ሰጭዎች ገልፀዋል፡፡ ከቡድን ተወያዮች አንዱ መምህር

*"እኔ ስለ ኩረጃ በጣም ያዘንኩትና እንደልማድ እየተቆጠረ መሆኑን ያረጋገጥኩት የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወቅት ከወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ተወክለው የመጡ ባለሙያዎች ጎበዝ ተማሪዎችን ሰብስበው መልስ እንዲሰጡና እንዲያስኮርጁ አቅጣጫ ሰጠው ሲሄዱ ነው፡፡"*

በማለት ገልጿል፡፡ ሌላው ተወያይ መምህርም ይህን ለማጠናከር ሲገልፅ

*"በአንድ የትምህርት ዘመን 10ኛና 12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ለመፈተን ተመለመልኩና ወደ አንድ ትምህርት ቤት ተላክሁ፡፡ መጀመሪያ የ10ኛ ክፍልተማሪዎች ተፈተኑና ተጠናቀቀ በሁለተኛው ዙር የ12ኛ ክፍል ለመፈተን በፈታኝ መምህራን ላይ ግምገማ ይካሄዳል፡፡ በግምገማው ወቅት አንተ ተማሪዎችን አስጨንቀሃል*

*(አጥብቀህ ተቆጣጥረሃል) በሚል 12ኛ ክፍል እንዳልፈትን ተደረግሁ”*

በማለት መረጃ ሰጧል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ50% እና በላይ ሁሉም ተማሪ (100%) እንዲያመጣ መታቀዱና ከመምህራን ጀምሮ እስከ ክልል ባለስልጣናትና ባለሙያዎች መገምገሚያቸውና መወዳደሪያቸው የተማሪዎች የማለፍ ቁጥር እንደ አንድ ትልቅ መስፈርት መሆኑ ጎላ ብሎ የቀረበ መወያያ ነበር፡፡ እንደመረጃ ሰጭዎች መምህራን እንዴት አድርገው አስተማሩና መዘኑ ሳይሆን ሁሉንም ከ50% እና በላይ እንዲያመጡ ያደረገ መምህር ይሸለማል፣ የስራ አፈፃፀም ውጤቱም ከፍተኛ ይሰጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በደንብ አስተምሮ ከ50% በታች ተማሪዎች ውጤት ካላመጡ መምህሩ በየመድረኩ ይወቀሳል፡፡ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱም ዝቅተኛ በመሆኑ የደረጃ እድገት እንደማያገኝ በቡድን ውይይቱ የተነሱ ነጥቦች ናቸው፡፡

ይህንን ለማጠናከር አንዲት የፊዚክስ መምህርት በቡድን ውይይቱ አንስታ

*“እኔ በትምህርት ቤቱ አዲስ ተመድቤ የመጣሁ ነኝ፡፡ የማውቀውን በደንብ አስተምራለሁ በተቀመጠው የፈተና ፕሮግራም መሠረት ፈተናየን አጠናቅቄ ውጤት ሳስገባ 50% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች 48% ነበሩ፡፡ ርዕሰ መምህሩ ይሄ ምንድነው አለኝ፡፡ ማርክ አልኩት፡፡ አፈጠጠብኝ፡፡ ግራ ገባኝ፡፡ እነዚህን ተማሪዎች በክረምት አስተምረሽ ሁሉም ተማሪዎች 50% እና በላይ እንዲያመጡ ካላደረግሽ እንኳን በዘንድው ዓመት በሚቀጥለው ዓመትም የክረምት ትምህርትሽን አትሄጅም በማለት አስቀርቶኛል”*

በማለት ተናግራለች፡፡

በትምህርት የተገኘ ውጤት የሚሰጠው ዋጋ አነስተኛ መሆን አንድ የኩረጃ ምንጭ እንደሆነ መምህራን በውይይቱ ገልጸዋል፡፡ ለዚህ እንደ ማስረጃ የሚያነሱት ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ ገብተው የተሻለ ውጤት ያመጡትም ሆነ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡት ለሥራ ሲወዳደሩ ልዩነት ያለመኖሩ፣ ይባስ ብሎም ለፈተና የሚቀርቡትን በውጤት ቅደም ተከተል ከማሳተፍ ይልቅ በእጣ ለውድድር እንዲቀርቡ ይደረጋል ብለዋል፡፡ ስለዚህ ጎበዝ ተማሪዎችም ለሰነፍ ተማሪዎች ያስቀዳሉ፡፡ ለማጥናት ያላቸው ፍላጎትም የቀዘቀዘ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተመራቂ ተማሪዎች በሙያቸው ወደ ስራ ያለመሰማራታቸው ኩረጃን እንደሚያባብስ መልስ ሰጠዋል፡፡ ስለዚህ ከፍተኛ ውጤት መጣም አልመጣም ለውጥ የለውም ብሎ ማሰብ የኩረጃ መንስኤ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

የወላጆች ድጋፍና ክትትል አነስተኛ መሆን የኩረጃ ምንጭ ነው በማለት መምህራን ጠቅሰዋል፡፡ በአብዛኛው ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸውን እንጅ በትክክል ትምህርት ቤት ሙሉ ጊዜያቸውን ተጠቅመው መማራቸውን፣ ትምህርት ቤት ሄድን ብለው የት እንደሚውሉ፣ ጓደኞቻቸው እነማን እንደሆኑ፣ ቤተ መጻሕፍት መጠቀማቸውን መረጃ በመያዝ አይከታተሉም፡፡ ተማሪዎችም ወላጆች አለመከታተላቸውን ስለሚያውቁ በደንብ ተግተው አይማሩም፣ አያጠኑም፡፡ በዚህም ምክንያት ለፅሑፍ ፈተና ኩረጃ የተጋለጡ እንደሆነ በየጊዜው ከተማሪዎች ጋር የሚውሉ መምህራን አብራርተዋል፡፡

ተማሪዎች በልቅ ጥያቄዎችና በቡድን ተኮር ውይይት የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ምንጮችን እንዲጠቅሱ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ በዚህም የተሰማቸውን ሲዘረዝሩ፡- ኩረጃ በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር ላይ የሚያስችለውን አስከፊነት በጥልቀት አርቆ ያለማሰብና ያለመገንዘብ እንደ ትልቅ ምክንያት አቅርበዋል፡፡ ከመንጃ ፈቃድ ጀምሮ እስከ ትልልቅ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃዎች ድረስ የሀሰት ማስረጃ መስፋፋት፣ ሰው በጥረቱ ለፍቶ አንብቦ ውጤታማ ከመሆን ይልቅ ሳይሰሩ በመኮረጅ

ውጤት ማምጣትን መምረጥ፣ በራስ የመተማመን ስሜት በመጥፋቱ ምክንያት በአብዛኛው ተማሪዎች ከኩረጃ ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም። በቡድን ተኮር ውይይቱ አንዱ ተማሪ *"ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች እኛ ሳንኮርጅ ብንቀር ሌላው ይበልጠናል በማለት እና የሠሩትን ለማረጋገጥ፣ አነስተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ከክፍል ክፍል ለማለፍ፣ መካከለኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች እኛ ባንኮርጅ እንጎዳለን በሚል አስተሳሰብ ይኮርጃሉ።"*

በማለት በአብዛኛው ተማሪዎች ለኩረጃ ዝግጁ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። በመቀጠልም ይኸው ተማሪ "አሁን የሚያስፈራው የሚያስቀዳ ወይም የሚያስኮርጅ ተማሪ የጠፋ እንደሆነ ይህች ሀገር ምን ልትሆን ነው" በማለት አጠቃሏል። በዚህ መረጃ መሰረት ምን ያህል የከፋ ችግር እያንዣበበ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ከፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤዎች እና ስለ ጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ህግና ደንብ በተመለከተ ለርዕሰ መምህራን በቃለ መጠይቅ ተሳትፈው ነበር። ለዚህ ጥያቄ በአብዛኛው ርዕሰ መምህራን የተቀራረበ መልስ የሰጡ ሲሆን ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የኩረጃ ምንጮች ናቸው ብለው ከጠቀሷቸው ውስጥ፣ ለዚህ ዋነኛው መንስኤ መንግስት ነው ይላሉ። ለዚህ እንደመገለጫ የጠቀሱት ትምህርት ቤቶች የሚወዳደሩት ከክፍል ክፍል ባለፉ ተማሪዎች ቁጥርና 50% እና በላይ ባመጡ ተማሪዎች ቁጥር ነው። መምህራንም የሚገመገሙት በሚያከናውኑት የመማር ማስተማር ሂደት ሳይሆን በተማሪዎች የቁጥር ውጤት ላይ እንደሆነ አብራርተዋል።

የተማሪዎች ተስፋ መቁረጥ ሌላ የኩረጃ ምክንያት እንደሆነ ሲገለጹ ውጤት ባመጣም ባላመጣም ለውጥ የለውም ብሎ ማሰብ፣ ብመረቅም ሥራ ስለማላገኝ ከአሁኑ መንጃ ፈቃድ ለማውጣት ከጠቀመኝ ለምን አጠናለሁ ማለት፣ በየትምህርት ቤቱ የወንበር እጥረትና በአንድ ክፍል ከመጠን በላይ የሆኑ ተማሪዎች መኖራቸው እንደ አንድ የኩረጃ ምንጭ ሆኖ ተጠቁሟል። በቃለ ምልልሱ አንዱ ርዕሰ መምህር ሲናገሩ

*ኩረጃን የሚጸየፍ ህብረተሰብ እንፍጠር፣ ኩረጃ ሳይሰሩ መክበርና ለሙስና ያጋልጣል እየተባለ በየሚዲያው ይነገራል በተግባር ሲታይ ግን ውሸት ነው። በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም የትም/ት ቤቱ አመራርና መምህራን ተወያይተን በመወሰን ስፔሻል ክላስ ውስጥ በክፍል 30 ተማሪ ብቻ ሆኖ የተሻሉ ተማሪዎችን ስንፈትን ሌሎች ተማሪዎች በመጮህ እንደመብት እኛ እንደሀገር አንጠቀምም ወይ በማለት ከፍተኛ ተቃውሞ ነበር። ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ከዞን እስከ ወረዳ ድረስ ተወቅሰናል። በዚህም በዞን ደረጃ በነበረው ውድድር ከ9-10ኛ ክፍል ካሉ 29 ትም/ት ቤቶች የመጨረሻ ደረጃ (29ኛ) ወጠናል። በየስብሰባውና በየመድረኩ የእኛ ስም በድክመት ስንወቀስ ከረምን። በ2005 ዓ.ም ስፔሻል ክላስ መፈተኑን ስናቆም ከ9-10ኛ ካሉ ክፍሎች ስንወዳደር 50% እና በላይ 99% በማስመዝገብ 3ኛ ስንወጣ ከ11ኛ - 12ኛ ክፍል 100% በማስመዝገብ 1ኛ ወጣን።*

በማለት ምን ያህል ወደ ከፋ ችግር እየሄድን መሆኑን አሳይቶናል።

ወጥ የሆነ የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ህግና ደንብ ያለመኖርና በትምህርት ቤት ደረጃ የወጣውን ህግም ተግባራዊ ለማድረግ አለመቻል ሌላ የኩረጃ መባባስ ምክንያት እንደሆነ ተገልጿል። በየትምህርት ቤቱ ያሉ ዶክመንቶችን በመፈተሽ በተገኘው መረጃ መሰረት በሁሉም ትምህርት ቤቶች የተለያየ ህግና ደንብ መኖሩን ያሳያል። ለአብነት ያህልም በሦስት ትምህርት ቤቶች ያለው ዶክመንት እንደሚያሳየው በአንደኛው ትምህርት ቤት፣ በቁራጭ ወረቀት መልስ ይዞ ሲኮርጅ የተያዘ 75% ከውጤቱ ይቀነሳል፡ ከጎን ወይም ከፊት ካለው ከኮረጀ 60% ይቀነሳል፣ የሚያስቀዳ ተማሪ 50% ይቀነስበታል፣ ስም ቀይሮ የተፈተነ ወይም ያስፈተነ እንዲሁም በሞባይል መልስ የተቀበለ ውጤቱ ይሰረዝና በዲሲፒሊን ኮሚቴ ቀርቦ ይቀመጣል፣ የሌላ ተማሪ ሲፈተን ከተገኘ በፍርድ ቤት ይከሰሳል ይላል። በሁለተኛው ትምህርት ቤት የተገኘው መረጃ በፈተና ወቅት ለሚያስቀዳ ተማሪ 80%

ውጤቱ ይቀንሳል፣ ለሚቀዳው ደግሞ 50% ውጤቱ ይቀንሳል። ሦስተኛው ትም/ት ቤት ያለው ዶክመንት የሚያሳየው ደግሞ የኮረጀ ወይም ያስኮረጀ ተማሪ እኩል 50% ውጤታቸው ይቀነሳል የሚል ነው።

የኩረጃ ህግና ደንብን በተመለከተ ከሀገር አቀፍ ወይም ከክልል ወይም ከዞን ወይም ከወረዳ ትም/ት ጽ/ቤት የተላከ የሌለ ሲሆን በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች የኩረጃ ችግር ሲፈጠር እንደሁኔታው እያዩና እየወሰኑ የሚያስተናግዱ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የመምህራን ግዴለሽነትና አጉል ተወዳጅነት ወይም ፍርሃት ለፅሑፍ ፈተና ኩረጃ መንስኤ ቀላል የማይባል እንደሆነ ጠቅሰው ይህ ግን አብዛኛውን መምህራን የማይወክል እንደሆነ ተናግረዋል። አንዳንድ መምህራን መንግስት የተወውንና ያመቻቸውን እኛ ብንቆጣጠር ምን ዋጋ አለው በማለትና በሌላ ትምህርት ቤትና ክልል የፈተናው ቁጥጥር ልቅ ስለሆነ የእኛን ተማሪዎች መጉዳት ነው ብለው በማሰብ ቁጥጥራቸው የላላ መሆኑን ይገልፃሉ።

**ሰንጠረዥ 3.** የተለያዩ የምዘና አይነቶች ለፅሑፍ ፈተና ኩረጃ ያላቸው ምቹነት በተመለከተ

| ተ.ቁ | የፈተና አይነቶች ለኩረጃ ባላቸው ምቹነት በደረጃ ሲቀመጡ | መረጃ ሰጭዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መምህራን | | | | | | | | | | ተማሪዎች | | | | | | | | | |
| | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | ምቹ አይደለ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | ምቹ አይደለም | |
| | | የድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 1 | እውነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች | 64 | 75.3 | 13 | 15.3 | 5 | 5.9 | 3 | 3.5 | - | - | 89 | 65 | 37 | 27 | 11 | 8 | - | - | - | - |
| 2 | የምርጫ ጥያቄዎች | 26 | 30.6 | 47 | 55.3 | 8 | 9.4 | 4 | 4.7 | - | - | 53 | 38.7 | 74 | 54 | 7 | 5.1 | 3 | 2.2 | - | - |
| 3 | አዛምድ ጥያቄዎች | 33 | 38.8 | 24 | 28.2 | 16 | 18.8 | 10 | 11.8 | 2 | 2.4 | 68 | 49.6 | 41 | 29.9 | 23 | 16.8 | 5 | 3.6 | - | - |
| 4 | አጫጭር መልስ የሚጠይቁ | 3 | 3.5 | 5 | 5.9 | 8 | 9.4 | 58 | 68.2 | 11 | 12.9 | 2 | 1.5 | 4 | 2.9 | 17 | 12.4 | 80 | 58. | 34 | 24. |
| 5 | ማብራሪያ የሚፈልጉ | 1 | 1.2 | 2 | 2.4 | 2 | 2.4 | 10 | 11.8 | 70 | 82.4 | - | - | - | - | 7 | 5.1 | 38 | 27. | 92 | 67. |

ከላይ በሰንጠረዥ 3 መምህራንና ተማሪዎች ለጽሑፍ ፈተና ኩረጃ የተጋለጡ የምዘና ዘዴዎችን እንዲለዩ በቀረበላቸው ጥያቄ መሠረት የእውነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች ለጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ያላቸው ምቹነት በጣም ከፍተኛ እንደሆነ 75.3% መምህራንና 65% ተማሪዎች መልስ ሰጠዋል። የምርጫ ጥያቄዎች ደግሞ ለኩረጃ የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ከግማሽ በላይ የሆኑ መረጃ ሰጭዎች (55.3% መምህራንና 54% ተማሪዎች) መልሰዋል። የአዛምድ ጥቂዎች ለጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ያላቸውን ምቹነት በተመለከተ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው መምህራን (38.8%) እና ተማሪዎች (49.6%) በጣም ከፍተኛ መሆኑን መልሰዋል። አጫጭር መልስ የሚጠይቁ የፅሑፍ ፈተናዎች ለፅሑፍ ኩረጃ ምቹነታቸው ዝቅተኛ መሆኑ 68.2% መምህራንና 58.4% ተማሪዎች መልስ ሰጠዋል። በመጨረሻ ማብራሪያ የሚጠይቁ የፅሑፍ ፈተናዎች ለኩረጃ ምቹ እንዳልሆኑ 82.4% መምህራንና 67.2% ተማሪዎች መልስ ሰጠዋል።

## 4. የጥናቱ ማብራሪያ፣ መደምደሚያና፣ የመፍትሄ ሀሳብ

### 4.1. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

በእኛ አገርም ሆነ በሌሎች አገሮች ያለው የትምህርት ስርዓት የተማሪዎችን አቅምና ብቃት የሚመዘኑበት መንገድ የጽሑፍ ፈተና ነው (Okoro,2001)፡፡ በዚህ የምዘና ዘዴ የሚፈጸምን ኩረጃ ለመከላከል ጥረት ቢደረግም መንስኤው የተወሳሰበና በየጊዜው እየተቀያየረና እየተስፋፋ በመጣው የኩረጃ ዘዴ ምክንያት ማስቆም አልተቻለም፡፡ ስለዚህ በየጊዜው በጥናት የተደገፈ መፍትሔ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም በተማሪዎች የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ በተደረገው ጥናት የተደረሰባቸው ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው በመረጃ ሰጭነት የተሳተፉት ተማሪዎች፤መምህራንና የትም/ት ቤት ርዕስ መምህራን የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ በተማሪዎች ላይ የሚያስከትለውን ችግር በአብዛኛው ከጠቀሷቸው መካከል ኃላፊነት የጎደላቸውና ለሙስና የተጋለጡ ዜጎችን ያፈራል፣ በራስ የማይተማመንና የተወዳዳሪነት መንስፈን ያዳክማል፣ ስራ አጥነትና ወንጀለኝትና ያባብሳል፣ በሥራ ሳይሆን በአቋራጭ ሳይለፉ መክበርን ያበረታታል፣ በትምህርት የሚገኝ ውጤትን ዋጋ ያሳጣል የሚሉ ናቸው፡፡ ይህ ግኝት በአሜሪካዊያና ሩስያውያን ኮሌጅ ተማሪዎች ላይ ከተደረገው ጥናት Lupton & Chapman (2002) ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በዚህ ጥናትም የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ የትምህርት ጥራትን በማሰናከሉ ምክንያት በተማሪዎች በራሳቸው፣ በማህበረሰቡና በሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳለው ተጠቅሷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Hamzeh (2012) የተባሉ ፀሐፊ ኩረጃ የትምህርትን ውጤት ዋጋ በማሳጣት በማህራዊና በስነ ልቦና ላይ የሚያስከትለውን የአመለካከት ችግር አብራርተዋል፡፡ ስለዚህ በሀገራችን ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት እርከኖች እንደልማድ እየተወሰደ ያለው አመለካከት ለማስወገድ የሚያመጣውን መዘዝ በደንብ መረዳትና መፍትሄ መፈለግ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

የፅሑፍ ፈተና ኩረጃ ዘዴዎችን በተመለከተ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ዋና ዋና ስልቶች የተባሉት፣ መልስ በቁራጭ ወረቀት ማስተላፍ፤ ከጎን ከሚፈተን ጓደኛ መጠቀም፣ በተለያዩ ነገሮች ቀድሞ ፅፎ መግባት፣ መግባቢያ ኮድ በመፍጠር፣ ቴክኖሎጅን በመጠቀም በሞባይል የስልክ መልዕክት በመቀያየር የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ግኝት Richard (2009) የሚባሉ አጥኚ ካገኙት ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ በአጥኚው የተገኙ ዘዴዎች ከጎን ከተቀመጡ ጓደኞቻቸው መልስ በመውሰድ፣ የመልስ መስጫ ወረቀት መቀያየር እና የተለያዩ ቀለሞችን፣ ጣታቸውንና ቅርጾችን እንደመግባቢያ ምልክት (ኮድ) በመጠቀም በሚል ተዘርዝረዋል፡፡ Coalter, Lim & Wanorie (2007) የላይኛውን ሀሳብ የተጋሩ ሲሆን ተማሪዎች በየጊዜው የተለያዩ የጽሑፍ ኩረጃ ዘዴዎችን በመጠቀም ምን ያህል ችግሩ አሳሳቢ እየሆነ እንደመጣ አሳይተዋል፡፡

የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ደረጃው ይለያይ እንጅ ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን ያለ ችግር ቢሆንም የችግሩ ምንጭ ደግሞ የተለያዩ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በዚህ መሠረት የጥናቱ ግኝት እንዳስቀመጠው የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ግን ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ከሚጠበቀው ስታንዳርድ በላይ ቁጥር ያላቸው ሆነው መማራቸውና መፈተናቸው ነው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች በደንብ ያለማጥናትና ፍላጎት ያለመኖር፣ ኩረጃን ለመከላከል ጠንካራ ህግ ያለመኖርና ተግባራዊ ያለማድረግ፣ አንዳንድ መምህራን የሀቅም ችግርና ግዴለሽነት፣ በተማሪዎች የቁጥር ውጤት ላይ ያተኮረ ተገቢ ያልሆነ ውድድር ናቸው፡፡

ይህ ግኝት በሱማሊያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሁለተኛ ደረጃ ትም/ት ቤቶች ካደረጉት ጥናት (Abdulah Muhammed, 2014) ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ አጥኚው ለኩረጃ ዋና ምንጮች ብለው ያነሷቸው የተማሪዎች የዝግጅትና የሀቅም ማነስ፣ ከፍተኛ ውጤት መፈለግ እና

የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ትኩረት ያለመስጠት ናቸው፡፡

አንድ ሌላ Cizek (2003) የሚባሉ አጥኝ የኩረጃ ምንጭ ብለው ያገኙት በአንድ ክፍል ውስጥ ከመጠን በላይ ቁጥር ያላቸው መፈተናቸው፣ ተማሪዎችን ለመማር የሚያነሳሱ ምቹ አካባቢዎች ያለመኖር፣ የመምህራን ለማስተማርና ተማሪዎችን ለመረዳት ያላቸው ፍላጎት ማነስ ነው በማለት ይጋራሉ፡፡

ሌላው በጥናቱ የተገኘው የጽሁፍ ፈተና ኩረጃ እንዲባባስ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ የፅሑፍ ፈተና ሲዘጋጅ በአብዛኛው ዝግ ጥያቄዎች (እውነት ወይም ሀሰት፣ ምርጫ፣ አዛምድ) መሆናቸውና የተግባር ልምምድና ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ግን አነስተኛ መሆናቸው ነው፡፡

## 4.2. ማደማደሚያ

ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶችንና ማጣቀሻ ጽሑፎችን እንዲሁም መረጃ ተሰብስቦ የተደረሰባቸውን የጥናት ግኝቶች መሠረት በማድረግ የሚከተለው ማደማደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

የጽሑፍ ፈተና ኩረጃ በሀገራችን እንደሰደድ እሳት በፍጥነት እየለበለበ ያለ በሌላ በኩል ደግሞ ችላ ተብሎ እንደልማድ የተያዘ አደገኛ የሆነ ለአሁንና ለወደፊት እድገታችን ፀርና ስጋት በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተማሪዎችንና መምህራንን ጨምሮ የፅሑፍ ፈተና ኩረጃን አስከፊነት የተገነዘቡ ቢሆንም ከችግሩ ለመውጣትና ለመከላከል ግን ተሳትፏችን በጣም አነስተኛ ነው፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለፅሑፍ ፈተና ኩረጃ እየተባባሰ መምጣት ትልቁን ድርሻ የሚይዘው መንግስት ነው፡፡ ለአብነት ያህልም መምህራን፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወረዳዎች፣ ዞኖችና ክልሎች የሚሸለሙትና የሚያበረታቱት ተማሪዎችን በማብቃት ሂደት ላይ ሳይሆን ባሳለፉት የተማሪ ቁጥር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መንግስት የትምህርትን ተደራሽነት የማስፋፋትን ያህል በትምህርት ጥራት ላይ ብዙ ያለመስራት፣ በትምህርት ቤቶች በቂ ግብዓት ያለመኖር፣ ውጤታማ የሆኑ መምህራንና ተማሪዎችን የሚያበረታታ ስርዓት ያለመኖር፤ ብቃት የሌላቸው መምህራንና ርዕሰ መምህራን መመደብ ለጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

ግኝቱ እንደሚያመለክተው የመምህራን የሀቅም ችግር እንዳለ ሆኖ መምህራን በግዴለሽነትና በአጉል ተወዳጅነት እንዲሁም ችግር ይደርስብኛል ብለው በመፍራት ተማሪዎች በጽሑፍ ፈተና ሲኮራጁ ያለመቆጣጠርና አንዳንዴም እንዲኮርጁ በማመቻቸት ያላቸው ድርሻ የሚናቅ አይደለም፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን በምግብ፣ በልብስ፣ በማዝናናት የሚንከባከቧቸውን ያህል የትምህርት ቤት ውሏቸውን፣ ጓደኞቻቸውን፣ የትምህርት አቅማቸውንና ጥረታቸውን ለማወቅና ለማገዝ ያላቸው ክትትል ዝቅተኛ ነው፡፡ የምዘና ስርዓታችንም ቢሆን የጽሑፍ ፈተና ኩረጃን ለማበረታታት ቀላል ሚና የለውም፡፡ የፈተናዎች አወጣጥ በየደረጃው የተማሪዎችን አቅም (ከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ የመረዳት ችሎታ) ያላገናዘበና ማብራሪያና የተግባር ክህሎትን የሚጠይቁ ፈተናዎች ላይ ያለማተኮር እና አነስተኛ ዋጋ መስጠት ለኩረጃ በር ከፋች መሆኑን ያሳያል፡፡

## 4.3. የመፍትሔ ሀሳቦች

ጥናቱ ከደረሰባቸው ማደማደሚያዎች፣ ከማጣቀሻ ፅሑፍ ከተገኙ መረጃዎችና ከተመራማሪዎች ልምድ መነሻ በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

የጽሑፍ ፈተና ኩረጃን ለመከላከልና ከተከሰትም በኋላ ተገቢ እርምጃ ለመውሰድ ትልቅ ኃላፊነት ያለበት መንግስት ስርዓት መዘርጋት ይጠበቅበታል፡ ፡ በዚህም መሠረት ከመጀመሪያው ሲታቀድ በተማሪዎች የቁጥር ውጤት ላይ ብቻ ሳይሆን የመማር ማስተማር ሂደቱን ማለትም የመምህሩን የጊዜ አጠቃቀም፣ የማስተማር ዘዴ፣ በሚያስተምረው ትምህርት ያለው ብቃት፣ የምዘና

ስርዓት፣ ተማሪዎችን በተግባር የማገዝና የመከታተል ክንውንን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በየደረጃው የሚደረግ ተገቢ ያልሆነ ውድድርም እንደገና የሚፈተሽበት ስርዓት ቢኖር፡፡ የተማሪዎች ስም ቅያሬ የጽሑፍ ፈተና ኩረጃን ከመከላከል አንፃር ታይቶ ህግ ቢወጣለት፣ ከጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ጋር በተያያዘ በየደረጃው ያለ የትምህርት አመራር፣ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ከፈተና ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት መዘርጋትና ወንጀልም በመሆኑ ሀገራዊ የሆነ ህግና ደንብ ተዘጋጅቶለት ተግባራዊ ቢሆን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በራሳቸው ሰርተው ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማበረታቻ ስርዓት ቢዘጋጅ ኩረጃን መከላከል ይቻላል፡፡

ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ጎበዝ፣ ስርዓት ያላቸው ሆነው እንዲያድጉ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ በመንግስት፣ በርዕሰ መምህራንና በመምህራን ብቻ ውጤት የሚመጣበት አይደለም፡፡ ስለሆነም ወላጆችም ሆነ አሳዳጊዎች በትክክል ክፍል ውስጥ ገብተው ሲማሩ መዋላቸውን፣ ትምህርታቸውን በደንብ መከታላቸውን፣ ከትምህርት ቤት ወጥተው የት እንደሚውሉ፣ ጓደኞቻቸው እነማን እንደሆኑ መረጃ በማሰባሰብ የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት ሀቅምን መሠረት ባደረገ በማሟላት በርትተው እንዲያጠኑና ያልሰሩትን ከሌሎች እንዳይፈልጉ በየጊዜው ማስገንዘብና ተከታትሎ ለውጤት ማብቃት ይገባል፡፡

ሁላችንም እንደምንረዳው የመምህርነት ሙያ የህሊና ስራ ነው፡፡ ልጆቹን አደራ ብሎ የሰጠንን ወላጅ፣ ህብረተሰብ፣ ሀገር ማሰብ እንዲሁም የተማሪው የወደፊት እጣ ፈንታው በመምህራን የሚወሰነውን ተማሪ በየጊዜው ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ጊዜያዊ ጥቅምና መንገራገር ተስፋ ሳያስቆርጣቸው የትምህርቱ ባለቤት ነን በሚል ተማሪዎችን በሚቻለው ሁሉ የተሻሉ እንዲሆኑ መርዳትና ከዚህም ባለፈ የሚኮራረጁ ተማሪዎችን ስለ ኩረጃ አስከፊነት ማስገንዘብ፣ መቆጣጠርና ለሚመለከተው ማሳወቅ ይጠበቃል፡፡ የተማሪዎችን አቅም ያገናዘበ የተለያዩ ጥያቄዎች ማውጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉት የሚለካና ማብራሪያ የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ከፍተኛ ዋጋ እንዲኖራቸው በማድረግ ማዘጋጀት የጽሑፍ ፈተናን ለመከላከል አንዱ መፍትሔ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ተማሪዎችም የነገ ሀገር ተረካቢዎችና ገንቢዎች መሆናቸውን አውቀው ጥቅሙና ጉዳቱ የራሳቸው ስለሆነ ኩረጃን መጥላትና ለሌሎችም ያለመተባበር እንደዜጋ ድርሻን እንደመወጣት ይቆጠራል፡፡

## ምስጋና

በመጀመሪያ ለሀገራችን ሰላምና እድገት ትልቅ እንቅፋት የሆነውን የተማሪዎች የፅሁፍ ፈተና ኩረጃ ዙሪያ ጥናት በማድረግ ሌሎች ተገንዘበው ኩረጃን እንዲከለክሉ የበኩላችንን እንድንወጣ ያሳሰበንን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡ በሁለተኛ በዚህ ርዕሰ ጥናት ለማድረግ ስናቅድ በጀት የፈቀደልንን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲን ከልብ እናከብራለን፡፡ በመጨረሻም ሙያዊ ግዴታን ለመወጣት በግልጸኝነት በጽሑፍ ፈተና ኩረጃ ዙሪያ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ለሰጡን የናሙና ትም/ት ቤቶች ርዕሰ መምህራን፣ መምህራንና ተማሪዎች ምስጋናችን ይድረሳቸው፡፡

## ዋቢዎች

ያለው እንዳወቀ (2011) የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ፡፡

Abdulah Muhammed (2014).Students' cheating during examinations in some selected secondary schools of liban zone,Somali regional state(unpublished MA thesis). Haromaya University.

Anteneh Assefa and Asres Berhan (2014).Cheating on examinations and its predictors among undergraduate students at Hawassa University College of medicine and health sciences. Research article. Hawassa: Ethiopia.

Aurora,A.C Teixeira, & Rocha, M.F. (2008). Academic cheating in Spain and Portugal: An empirical explanation. International Journal of Iberian studies.21 (1)

Best, J.W. and Kahn J.V. (2007), *Research in Education (9th ed.).*New Delhi: Prentice-Hall of India Private Limited.

Burns, R. (2000). *Introduction to Research Methods*. (*4th ed.)*.Long man.

Cheating in College why Students do it and what educators can do about it. The john Hopkins University press.

Cizek, J. C. (2003). Detecting and preventing classroom cheating: promoting integrity in assessment. USA: Corwin Press

Coalter, T., Lim, C.L., & Wanorie, T. (2007). Factors that influence faculty actions: A study on faculty responses to academic dishonesty. *International Journal for the Scholarship of Teaching and Learning*, *1(1)*.

Graves, M. S. (2008). Student Cheating Habits: A Predictor of Workplace Deviance. *Journal of Diversity Management*, *3(1)*.

Hamzeh, M. (2012).Undergraduate students' cheating in exams. Damascus university Journal ,28(1).

Lanier, M. (2006).Academic Integrity and Distance Learning. Journal of Criminal Justice Education 17(2).

Lupton, R., & Chapman, K. (2002). Russian and Americans college students' attitudes, perceptions, and tendencies toward cheating. Educational Research, 44(1).

Mahmoud ,I., & Fatima Al-Shaikh (2013). Factors that lead to cheating in exams and how to avoid them. GSTF International Journal of education. 1(2).

McCabe, D. and Drinan, P. (1999).Toward a Culture of Academic Integrity. *Chronicle of Higher Education*, 46(8).

Okoro, E.C. (2001). The impact of examination malpractice on the functionality of education in Nigeria. *International Journal of Administration, Planning & Research* 1(1).

Richard, J. (2009).Cheating in examinations: a study of academic dishonesty in a Malaysian college. Asian Journal of university education.5 (2).

Thibodeau, P. (2007). 'Cheating on IT Exams May Cast Doubt on Their Value', Computerworld 41(18)

Trevino, L. (2006). Academic dishonesty in graduate business programs: *Academy of management learning and education, 5(2)*.

Vandehey, M. Diekhoff, G, & LaBeff, E. (2007). College cheating: A twenty year follow up and the addition of an honor code. *Journal of College Student Development*, *48(4)*.

Wilson, B. (2008) Predicting Intended Unethical Behavior of Business Students. The Journal of Education for Business 83(4)

Zauwiyah, A., Maimun S., & Junaini M.(2008). Malaysian university students' attitudes to academic dishonesty and business ethics. *Asia Pacific Journal of Education*, *28(2)*.